# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 120 ነሃሴ 27 ቀን 2002 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**"የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:"**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው**

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔው አገዛዝ የርቀት ትምህርት በኢትዮጲያ እንዳይሰጥ ከለከለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት እንዳይሰጥ የከለከለ ሲሆን የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ህግና መምህራን ስልጠና ትምህርት እንዳይሰጡ አግዷቸዋል።

ይሄው ባሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባና በሃገሪቱ የተለያዩ ከተሞች አነጋጋሪ የሆነው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የሚመለከተው መመሪያ ርምጃው የተወሰደው በዘፈቀደ መሆኑን ይህም የተማሪዎችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስ የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ዜጎች ገልጸዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ምክትል ዋሾ የሆነው በረከት ስምዖንን ጨምሮ ሚኒስትሮችና ባለሥልጣናት ከኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ኢንስቲትዩት በትራንስፎርሜሽናል ሊደርሽፕ ኤንድ ቼንጅ በድኅረ ምረቃ በቅርቡ እንደሚመረቁ ለአገዛዙ ቅርበት ያለው የሪፖርተር ጋዜጣ ባለፈው ሳምንት መዘገቡ ይታወቃል። ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት የወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት የራሳቸውን የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪዎች በርቀት ትምህርት በገንዘባቸውና በስልጣናቸው በጃቸው ካደረጉ በኋላ ይህ አይነት ውሳኔ መተላለፉ ወያኔ ለዜጎች ምንም ቅንጣት ያህል ደንታ የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ እንደ አሜሪካ ቪ ኦ ኤ ሬዲዮ ዘገባ የቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ፕሬዚደንት "በግሉ ተቋማት የጥራት ችግር ያለባቸው እንዳሉ አይካድም፤ የሚያሳዝነው የዘርፍ ችግር ተደርጎ መወሰዱ ነው" ማለታቸውንም ታውቋል።

## የኢትዮጵያ ብር የምንዛሪ ዓቅም ዋጋ ከ20 በመቶ በላይ መውረዱ ታወቀ። እርምጃው የዋጋ ግሽበቱን በማናር የኑሮ ውድነቱን እንደሚያባብስ ይሰጋል

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነሃሴ 25 ቀን 2002 ባወጣው መግለጫ 13 ብር ከ 62 የነበረው አንድ የአሜሪካ ዶላር ኦፍሴላዊ ሚንዛሪ ወደ 16 ብር ከ67 ሳንቲም ዝቅ ማለቱ አስታውቆአል።፡ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ላይ ከመምጣቱ 1983 በፊት የአንድ የአሜሪካን ዶላር ሚንዛሪ ዋጋ 2 ብር ብቻ የነበረ ሲሆን ባለፉት 19 አመታት የብር ዋጋ በተከታታይ ቁልቁል እየወረደ መጥቶ አሁን ከደረሰበት 16 ከ 67 መድረሱ እጅግ የሚያሳስብ ነው ተብሎአል። አንዳንድ የገቢያ ሙያተኞች የአሁኑ የዋጋ ግሽበት እንደ ነዳጅና ማዳበሪያ የመሳሰሉ ከውጪ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ምርቶች ዋጋ እጅግ በማናር የህዝባችንን የሁሮ ደረጃ የባሰውኑ ገደል ውስጥ እንደሚጨምር እየተናገሩ ነው። በተለይ ከምርጫ 97 ወዲህ በተከታታይ ባለ ሁለት አሃዝ እድገት በማስመዝገብ ልማታዊ መንግሥትነቴን እያረጋገጥኩ ነውና አርፋችሁ ተገዙ እያለ የሚሰብከው ወያኔ እና ጀሌዎቹ ይህንን በአደባባይ አፍጦ የወጣውን የህዝቡን ኑሮ ደረጃ ወደ አስከፊነት የሚለውጠውን የምንዛሪ ማሽቆልቆል በተለመደው ቅጥፈት ለማስተባበል ልማታዊ እድገታችን ተከትሎ የመጣ በረከት ነው ብለው ሊሞግቱ እንደሚሞክሩ ይጠበቃል።

አዲሱ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሊያስከትል የሚችለውን ሥጋት ለማወቅ አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ተዘዋውሮ ያነጋገረው ዘጋቢያችን፤ ወያኔ የውጭ ምንዛሪ እጥረት በገጠመው ቁጥር እየተነሳ የሚያወጣው የተመን አዋጅ በተለይ በከተሜው ነዋሪና በሸምቶ አዳሪው ህብረተሰባችን ላይ ከፍተኛ የሆነ የዕቃ ዋጋ ንረትን ስለሚያስከትል ኑሮን ከዲጡ ወደ ማጡ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለመኖር ሲል ነጻነቱንና ክብሩን ሰውቶ የነበረውን ህዝብ በማስቆጣት ለሥር ዓቱ መውደቂያ ጉድጓድ መማሻም ሊሆን ይችላል መባሉን ዘግቦአል።

## የአዲስ አበባ አሽከርካሪዎች በአገዛዙ የትራፊክ ፖሊሶች በደል እየደረሰብን ነው በማለት አማረሩ

የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የትራፊክ ፖሊሶች ፍጹም አግባብነት በሌለው መልኩ ያለምንም ምክንያት ቅጣት እየቀጧቸው መሆኑን ና በዚህም ምክኒያት እጂግ እየተማረሩ መሆናቸውን በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አሽከርካሪዎች ለዘጋቢያችን ገለጹ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ይህ ችግር በአብዛኛው ጎልቶ የታየው በታክሲ አሽከርካሪዎች ላይ መሆኑንና የትራፊክ ፖሊሶቹ ለአገዛዙ ገንዘብ በዚህ መንገድ ሰብስቡ የተባሉ እስኪመስሉ ድረስ ምንም ስህተት ባልተሰራበት ሁኔታ ቅጣት እየቀጧቸው መሆኑ በጂጉ እንዳበሳጫቸው ተናግረው ፖሊሶቹ ያላግባብ አሽከርካሪዎቹን ሲቀጡ አቤት የሚባልበትም ሆነ የሚዳኙበት አለመኖሩ ደግሞ ሌላው አሳዛኝ ነገር እንደሆነባቸው ተናግረዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በሃገራችን የተለያዩ ሴክተሮች ፍጹም የሆነ ዝርክርክነትና በሙስና የተዘፈቀ አሰራርን ሲያሰፍን መቆየቱንና እያሰፈነ ያለ መሆኑን በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን አይዘነጋም፡፡

## የወያኔ አገዛዝ የህዝብ ገንዘብ መዝረፉን እንደቀጠለ የአለም የምግብ ፕሮግራም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች የምግብ ጥገኞች መሆናቸውን ገለጸ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካል የሆነው የአለም የምግብ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ጽህፈት ቤት ባወጣው ሪፖርት በያዝነው የፈረንጆች አመት 9.4 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የእርዳታ ጥገኞቹ ሆነው እንደቆዩ አስታውቋል።

ድርጅቱ፥ ከጥር እስከ ታህሳስ ላለው ጊዜ 880 ሺህ ሜትሪክ ቶን እህል እንዳስፈለገ እና ይህም በገንዘብ ሲሰላ 652 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ወይም ከ8.8 ቢሊዮን ብር በላይ) እንደሆነ ገልጿል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ "ፍሬን ሎቢንግ ዳት አርግ" የተባለ እና የአለም መንግስታት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ለማድረግ የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች እየተከታተለ የሚያወጣ ድረ-ገጽ የወያኔ አገዛዝ ለዚህ ጉዳይ ያፈሰሰውን የገንዘብ መጠን አጋልጧል። እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2007 እና 2008 ብቻ የወያኔ አገዛዝ ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ በአሜሪካን አገር ለሚገኙ ተሚጋቾች መክፈሉ ታውቋል። ከተሚጋች ድርጅቶቹ ውስጥ የከዚህ ቀደም ተደጋጋሚ ዘገባዎቻችን ርእስ የነበረው ዲ.ኤል.ኤ ፓይፐር ከግማሽ በላይ የሆነውን ክፍያ መውሰዱም ታውቋል።

በጉዳዩ ላይ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የላኩ የፖለቲካ ተንታኝ፥ "ይህንንስ በቀጥታ ከአሜሪካ መንግስት ጋር የሚገናኝ ጉዳይ ስለሆነ በግልጽ አየነው፤ የወያኔ ባለስልጥናት የእርዳታ ጥገኛ ከሆነው ህዝብ ጉሮሮ እየነጠቁ በቀጥታ ወደ ኪሳቸው የሚያስገቡትን በአለም ዙሪያ ያሉ ባንኮች ይቁጠሩት" ብለዋል።

## የሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው አሰግድ ተፈራ አገር ጥሎ ወጥቶ በስደት እንደሚገኝ ታወቀ

ለረዥም አመታት የሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኖ ያገለገለው ጋዜጠኛ አሰግድ ተፈራ በተደጋጋሚ ሲደርስበት በነበረው ማስፈራሪያ፣ ድብደባና የግድያ ሙከራ ምክንያት መሰደዱን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አሳይቷል።

አሰግድ ተፈራ የሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅ በነበረባቸው አመታት በርካታ የሙስና ወንጀሎችን የሚያጋልጡ ዘገባዎችን በማጠናቀር የሚታወቅ ሲሆን፤ ከበርካታ ወራት በፊት የወያኔ ደጋፊ ከሆነው ሼክ አላሙዲን ኩባንያ ጋር የተያያዙ ተከታታይ ሪፖርቶችን ማቅረቡ ይታወሳል። ጋዜጠኛው ከደረሱበት ተደጋጋሚ ዛቻዎች እና ድብደባ በተጨማሪ ከነቤተሰቡ በሚኖርበት ቤት ላይ ቦምብ ሊጣል ሲል በጎረቤቶቹ እርዳታ መትረፉን ተናግሯል።

በመጨረሻም የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ሃላፊ የሆነው ብርሃኑ አዴሎ ጋዜጠኛው ሪፖርተርን ለቆ የሰነድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ እንዲሰራ እንዳስገደደው አስረድቷል። ሰነድ ጋዜጣ የብርሃኑ አዴሎ ንብረት እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል። ለአራት ወራት ያህል ግዳጁን ተቀብሎ ሰነድ ጋዜጣን በዋና አዘጋጅነት ማገልገሉን የገለጸው አሰግድ፤ አራስ ልጁን ጥሎ ከባለቤቱ ጋር መሰደዱን ተናግሯል።

## “ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ” የሁሉም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ትብብር የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው!!!

የአፋር ሕዝብ ፓርቲ፣ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነትና የፍትህ ንቅናቄ ተቀናጅተው **“ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያን”** መፍጠራቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብስረዋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ  የዚህ ጥምረት መሥራች አባል በመሆኑ የተሰማውን ደስታ በድጋሚ ይገልፃል።

በአገራችን የተንሰራፋውን ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ አስወግደን ለሁላችንም የምትስማማ አገር እንድትኖረን ለማድረግ በሁሉም የዲሞክራሲ ኃይሎች መካከል ጥብቅ ትብብር መፍጠር ግድ ነው። ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ይህንን ሃቅ ከተረዳን ውሎ ያደረ ቢሆንም እስካዛሬ ድረስ ዘላቂነት ያለው ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት ግን ሳንችል ቀርተናል። ይህ ጥምረት በዚህ ረገድ ለሚደረገው ሰፊ ትግል  መንገድ አመቻች ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ጥምረቱን የፈጠርን ድርጅቶች ከአሁን በኋላ እንደ አንድ ድርጅት ሆነን የምንደራደር በመሆኑ በመጠኑም ቢሆን የተደራዳሪዎችን ቁጥር በመቀነስ ረገድ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ሌሎችም ድርጅቶች እንደዚሁ በዓላማ ከሚመሳሰሏቸው ጋር ጥምረት ፈጥረው ቢመጡ የትብብር ፕረታችንን የበለጠ ፍሬዓማና ዘላቂ ያደርግልናል፤ ድካማችንንም ይቀንስልናል የሚል ፅኑ እምነት አለን።

ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያን የፈጠርን ድርጅቶች ወያኔን በጋራ ትግል አስወግደን በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን እስኪረከብ ድረስ አብረን ለመቆም ቃል ገብተናል። ጥምረታችንን አጠናክረን ወደ ውህደት ልናመራ የምንችልባቸውን መንገዶች ለመቀየስም ወስነናል። ውህደት እስኪፈጠር ድረስም በአንድ ድምጽ እንናገራለን፤ ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ ኃይሎቻችንን እናቀናጃለን።

እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት የታለመላቸውን ግብ ያልመቱ በርካታ የትብብር ፕረቶች ተደርገዋል። በዚህም ምክንያት ዛሬ የትብብር ጥያቄ ከየአቅጣጫው እየተነሳ ቢሆንም እንኳን በትብብሮች ዘላቂነት ላይ ሰዎች ጥርጣሬ ቢኖራቸው ሊገርመን አይገባም። ከአሁን በኋላ የምናደርጋቸው ትብብሮች ከቀድሞ ስህተቶቻችን የተማርን መሆናችንን የሚያሳዩ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህም ምክንያት ከመነሻው ጀምሮ ትብብሮቹ ሊያመጡት በሚፈልጉት ውጤትና በዘላቂነታቸው ላይ ግልጽ የሆነ መግባባት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ አገራችን እና በአጠቃላይ የአፍሪቃ ቀንድ የሚገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ እግምት ውስጥ በማስገባት ከድርጅት ፍላጎት አርቀን ትውልድን እያሰብን ለጋራ ትግል መዘጋጀት ይኖርብናል ብለን እናምናለን። ጥምረትን ስንፈጥር ይህን በልባችን ይዘን ነው።

ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ በአደረጃጀትም ሆነ በትግል ስልት የተለየ መንገድ ከያዙ ፀረ-ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ሁሉ ጋር ተባብሮ  ለመሥራት ያለውን ዝግጁነት ራሱን ባስተዋወቀበት መግለጫ ገልጿል። በዚህም መሠረት ጥምረቱ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ያለውን የትብብር አድማስ በማስፋት ሥራ ላይ ጠንክሮ ይሠራል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በዚህ ጥምረት የጀመረውን የትብብር ሂደት አጠናክሮ በመቀጠል ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ሁሉም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንዲተባበሩ ጥሪውን ያድሳል። ሁላችንም በጋራ ስንቆም በተቀናጀ ትግል በአጭር ጊዜ ወያኔን አስወግደን ፍትህ፣ እኩልነትና ነፃነትን እንደምናሰፍን እርግጠኞች ነን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የፍቅር ትርጉሙ

ከእለታት አንድ ቀን፥ በአንድ የስደት አገር ምሽት፣ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እራሳቸውን በሞቀ ክርክር መሃል ያገኛሉ። ክርክሩ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሲሆን፤ የአንድ የዝግጅት ክፍላችንን አባል ትኩረት የሳበው ርእስ በሁለት ወጣቶች መካከል የተካሄደው ልውውጥ ነው።

ወጣት ቁጥር 1፥ በአሁኑ ሰዓት አገራችን ያለችበት ሁኔታ አንገብጋቢ ስለሆነ፤ ማንኛውም ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ፈጣን፣ ጠንካራ እና ያለውን አደገኛ ሁኔታ የተረዳ ሊሆን ይገባዋል ይላል። ወጣት ቁጥር 2 ደግሞ፥ አይ ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ረጋ ብለን እየተካሄደ ያለውን ሁኔታ ልንመረምር እና ለምንስ እየተካሄደ እንደሆነ እራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል ይላል።

በዚህ ወቅት ወጣት ቁጥር 1 ለወጣት ቁጥር 2 ጥያቄ ያቀርብለታል። “እስኪ ይህንን ሁኔታ አስብ” ብሎ ጀመረ፥ ወጣት ቁጥር 1። “ከስራ መጥተህ፣ እቤትህ ደጃፍ ትደርሳለህ። ያላሰብከው ሁኔታ ይጠብቅሃል። በሩ ተሰብሯል። ትገባለህ። አንድ ወንበዴ እናትህን ሲደፍራት ታገኛለህ። መጀመሪያ የምታደርገው ነገር ምንድን ነው? የተቻለህን መንገድ ሁሉ ተጠቅመህ ወንበዴውን ማስቆም አይደለም?” ይለዋል።

ወጣት ቁጥር 2 እንዲህ ሲል መለሰ፥ “አይ! ‘ሰውየውስ እንደዚህ የሚያደርገው ለምንድን ነው?’ የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ እና መመለስ አለብን።”

በዚህ ወቅት ወጣት ቁጥር 1 በመገረም እንዲህ አለ፥ “ይኸውልህ ወንድሜ፥ ይቅርታ አድርግልኝ እንጂ...የእብድ ሰው ትርጉሙ ይህ ነው። ጤናማ ሰው እናቱ አይደለችም ማንኛውም ሰው እንደዛ እፊትለፊቱ እየተጠቃ ዝም አይልም። ወይም አንተ እንደምትለው መቀመጫ ፈልጎ ተቀምጦ ወንበዴው ምን ሆኖ ይሆን እንዲህ ያለ ነገር ሰው ላይ የሚፈጽመው ብሎ አይመራመርም። ጤናማ ሰው በዙሪያው ያለውን ነገር ፈጥኖ በማሰስ ወይ ዱላ ወይ ቢላዋ አንስቶ አጥቂውን በማጥቃት ተጠቂዋን ያድናል፤ ወደ ህክምናም ይወስዳታል። ህግ አስከባሪ ሃይል ጠርቶም ወንጀለኛውን ያስረክባል። ወደፊት እንዲህ አይነት ወንጀል እንዳይፈጸም ለመከላከል በሚል በወንበዴው ስነ-ልቦና እና ታሪክ ላይ መመራመር እና መፈላሰፍ ካስፈለገ፤ እሱን ኋላ ላይ ነገሮች በቁጥጥር ስር ከዋሉና ሰላም ከሰፈነ በኋላ ያደርጋል።” አለው።

በዚህ ጊዜ ወጣት ቁጥር 2 እና በክፍሉ ውስጥ የነበሩ ሌሎች ከመሳቅ ውጪ ምንም አልተባለም።

“የ1960ዎቹ ትውልድ” ተብለው የሚጠሩት ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ስር ነቀል ለውጥን ለማምጣት በነበራቸው የጋለ ስሜት በመነሳት በወቅቱ ያካሄዱት ትግል እና በሂደት ፈጽመውታል የሚባለው ስህተት፤ ጥቂት የማይባሉ የዚህ ዘመን ወጣቶችን በፍርሃት አደንዝዟል። “እኛም ለውጥን ለማምጣት እንፈልጋለን፤ እኛም መስዋእትነትን አንፈራም፤ ነገር ግን የአባቶቻችን ትውልድ የፈጸመውን ስህተት መልሰን እንዳንደግም ምን ዋስትና አለ?” ብለው የሚጠይቁ ጥቂቶች አይደሉም።

ይህ አደንዛዥ ፍርሃት ምክንያታዊነታቸውን የቀማቸው እና ግራ መጋባት ውስጥ የከተታቸውም ጥቂቶች አይደሉም። በመግቢያችን ላይ በጠቀስነው ታሪክ ውስጥ እንደነበረው ወጣት ቁጥር 2 እናታቸው ስትጠቃ ቢያዩ እንኳ አጥቂዋን አጥቅተው ማባረሩ ትክክለኛው እርምጃ ላይሆን ይችላል ብለው የሚጠራጠሩ፤ የተልፈሰፈሱ እና እረኛ እንደጠፋቸው በጎች በሃሳብ ጫካ ውስጥ የሚንከራተቱ አሉ። ዝምተኛነትን እንደ ሰላማዊነት የሚያዩ እና የፍቅርን ትርጉም የሚያዛቡም ብዙ ናቸው።

ይህ ደግሞ ይኸው በመግቢያችን የጠቀስነው የዝግጅት ክፍላችን አባል በአንድ ወቅት ከሌላ እጁን ከሰጠ ወጣት ጋር ወዳደረገው ውይይት ይወስደናል። የኛው ልጅ፥ “ወያኔን ድል መንሳት የሚቻለው እንዴት ነው?” ብሎ ወጣቱን ይጠይቀዋል። ወጣቱም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “ወያኔን ማሸነፍ የሚቻለው በፍቅር ብቻ ነው። እኔ ከዚህ በኋላ በጦርነት እና በሌላ ምንም አላምንም። በፍቅር ብቻ ነው።” አለው።

እኛ፥ ወያኔንም ሆነ ማንኛውንም አጥፊ ሃይል በፍቅር ማሸነፍ እንደሚቻል ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለንም። ፍቅር አሸናፊ ሃይል ነው። ነገር ግን የኛ የፍቅር ትርጉም እንደዛ እንደተንበረከከ ወጣት የተዛባ አይደለም። ፍቅር ማለት የወደድከው ሰው በጭንቅላትህ ላይ እንዲረማመድብህ መፍቀድ ማለት አይደለም። ፍቅር ምክንያታዊ የሆነ ስሜት እንጂ፤ እውርነት አይደለም። ፍቅር ያከብራል፤ መልሶ እንዲከበርም ይጠብቃል። ፍቅር ቸርነትን ያደርጋል፤ ይቅርም ይላል። ከልክ ባለፈ መንገድ ሲጠቃ ግን ቆሞ አያይም፤ ይልቁንስ እንደ እሳት ነበልባል ሆኖ ደግሞ ይባላል።

ፍቅር እናቱ ስትጠቃ ቆሞ አያይም። በሃያ ሁለት ጥይቶች ተበሳስቶ ሰውነቷ እንደ ወንፊት ሲሆን ያጠቋትን ወድቆ አይለማመጥም። ፍቅር የሰባት አመት ልጁ አይን በጥይት ሰደፍ ሲመታ ቆሞ አያይም። ፍቅር የአስራ አራት አመት ልጁ ተንበርክኮ እየለመነ ልቡ በጥይት ሲቀደድ ዝም አይልም። ፍቅር አገሩ የዘረኞች እና የወንበዴዎች መሳለቂያ እና መጨፈሪያ ሲሆን ቆሞ አያይም። ፍቅር ደንቆሮና እውር አይደለም። ፍቅር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቆጪና ተናዳጅም ነው። እንደዛ ያልሆነ ፍቅር፣ ፍቅር አይደለም፤ ድንዛዜ እንጂ።

አገሩን የሚወድ፣ እናቱን የሚወድ፣ ልጁን የሚወድ፣ ወንድሙን የሚወድ፣ እህቱን የሚወድ ቢኖር፤ ተቆጥቶ የመነሻው ዘመን አሁን ነው።

ከድንዛዜ እና ከግራ መጋባት ያድነን...የፍቅር ሰዎችም ያድርገን ብለን እየተመኘን፣ የዛሬዋን ሃተታችንን ባጭሩ እንቋጫለን።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## “የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ”

*(ከዝግጂት ክፍላችን)*

“በአይኑ ምሰሶ ይዞ ከሌላው አይን ጉድፍ ላውጣ ይላል”፤ “አመድ በዱቄት ይስቃል”...እና የመሳሰሉት፤ አባቶቻችን ከሃይማኖት እና ከልምድ ወስደው የባህል እና ቋንቋችን አካል ያደረጓቸው አባባሎች ናቸው። ሃፍረተ-ቢስነትን እና ግብዝነትን ይገስፃሉ። በሌሎች ከመፍረዳችን በፊት እራሳችንን አጥርተን እንድንመለከት ይጋብዙናል።

ዛሬ እነዚህን አባባሎች እንድናስታውስ ያደረገን፤ የወያኔ አገዛዝ በትምህርት ጥራት ስም የተልእኮ ትምህርትን አገደ የሚለው ዜና ነው። የአሜሪካ ድምጽ በጉዳዩ ላይ እንደዘገበው፥ በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሙሉ የተልእኮ ትምህርት መስጠታቸውን እንዲያቆሙ አዟል።

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቃል አቀባይ አበራ አባተ አበበ፥ እገዳው የተጣለው የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ ሲባል ነው እንዳለና ብዙ የግል ትምህርት ቤቶች ትርፍ ማግኘት እንጂ ጥራት ያለው ትምህርት የመስጠት ፍላጎት እንደሌላቸው መግለጹን የአሜሪካ ድምጽ በዘገባው አክሏል። ይህን ምክንያት እውነት ነው ብለን ብንቀበለው እንኳ፣ “ታዲያ የህዝብ ትምህርት ቤቶችስ ለምን ታገዱ?” የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ከዚህም በተጨማሪ፥ የግል ትምህርት ቤቶች የህግ እና የአስተማሪነት ዲግሪ ፕሮግራሞች እንዳያቀርቡ የታገዱበት ምክንያት አልተገለጸም። ይሁን እንጂ የዚህ ጽሁፍ ትኩረት ይሄ አይደለም።

በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር በምትገኘው ኢትዮጵያ፥ የትምህርት ጥራት ደረጃ፣ መሬት ነክቷል ብቻ ሳይሆን፣ አንዳንድ ቀልደኞች እንደሚሉት፣ መሬት ከወደቀም በኋላ ወደታች መቆፈር ጀምሯል። ይህ አሳዛኝ ሃቅ ብዙ የተወራለት ነው። የዛሬው ሃተታችንም ይህንን ሃቅ የሚከራከር አይደለም።

የወያኔ አገዛዝ ለትምህርት ጥራት ስል የተልእኮ ትምህርትን አገድኩኝ ማለቱ ግን በብዙ ምክንያት አስቂኝ ነው። አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች ለከፈላቸው ሁሉ ዝም ብለው ዲግሪ ይሰጣሉ ብሎ ተቆጪ ሆኖ መቅረቡም ፈገግ ያሰኛል። እነሆ በአይኑ ምሰሶ ይዞ ከሌላው አይን ጉድፍ ካላወጣሁ የሚለው ግብዝ ወይም አይን አውጣ ሰው ምሳሌ!

የዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ያውም የህዝብ ገንዘብ እያፈሰሱ፣ ለአንድ ዲግሪ እስከ አስር ሺህ የአሜሪካ ዶላር እየከፈሉ ከውጭ አገራት የተልእኮ ትምህርት ተቋማት የምስክር ወረቀቶች መሰብሰባቸው ይታወቃል። ያንን ሁሉ የህዝብ ገንዘብ አፍስሰው ቢማሩ ደግሞ አንድ ነገር ነበር። ይልቁንስ በስማቸው ፈተና እየወሰዱ እና የቤት ስራዎቻቸውን እየሰሩ የማለፊያ ውጤት የሚያስገኙላቸውን ሰዎች በጎን ይቀጥራሉ። የዚህ የወንበዴዎች ቡድን ቁንጮዎች ምሁራንን ከአገሪቱ በማሳደድ የአገሪቱን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወና አድርገው የትምህርትን ጥራት አፈር ማስበላታቸው ሳያንስ፤ በግላቸውም እንደዚህ ሲሳለቁ ቆይተዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት የትምህርት ደረጃን እና ጥራትን በሚመለከት ያልሰበሩትና ያልተረማመዱበት ህግ የለም። አንድ ሰው የመጀመሪያ ዲግሪ ሳይዝ ሁለተኛ ዲግሪ ሊኖረው አይችልም የሚለው የምህርት ሚኒስቴር ህግ፤ ባለፉት ሃያ አመታት የወያኔ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች መረማመጃ ሆኖ ቆይቷል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንኳ ያልጨረሱ ካድሬዎች ከውጭ አገር በህዝብ ገንዘብ የተገዛ የማስትሬት ዲግሪ ምስክር ወረቀት እየያዙ ወደየመንግስት መስሪያ ቤቱ በመግባት ያለብቃታቸው ስልጣን እና የደሞዝ ጭማሪ ሲንበሸበሹ ቆይተዋል። አሁን እነዚህ ዱርዬዎች ናቸው ለትምህርት ጥራት ዘብ ጠባቂ የሆኑት?!

መልስ ተሰጥቷቸው ብሔራዊ ፈተና ለመውሰድ የተቀመጡ፤ በውሸት ያገኙትን ከፍተኛ ውጤት አንጠልጥለው “ድንጋይ ፋብሪካ” የሚል ቅጽያ ስም ከወጣለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የገቡ እና እዛም ሄደው ተምረው ፈተና ማለፍ ስላልቻሉ መስፈርቱ ሁሉ ዝቅ ተደርጎላቸው በገፍ የተመረቁ። ድንቄም የምህርት ጥራት ጉድለት ተቆርቋሪዎች!

ለመሆኑ በተልእኮ ትምህርት ላይ የተደረገው እገዳ የውጭ አገሩንም ይጨምር ይሆን? ለነገሩ ቢጨምር ባይጨምር እነሱን ምን ገዷቸው። ማስትሬት ዲግሪ እንደሆነ እስካፍንጫ ተሰብስቧል።

እንግዲህ ውንብድና እና ዘረፋን የማንነቱ ማእከል ካደረገ ቡድን እንዲህ ያለ ሃፍረተ-ቢስነት እና ግብዝነት ቢመጣ አይገርምም። እኛም ስለጉዳዩ የምናወራው አገራችንን በጉልበት ተቆጣጥሮ ስላለው ስርአት ማንነት ለማስታወስ ብቻ ነው። ይህ፥ እየሰረቀ አትስረቁ፤ ህግ እየሰበረ ህግ አክብሩ፤ እየገደለ አትግደሉ፤ አገር እያፈረሰ ሌሎችን ጸረ-ሃገር፤ ህዝብ እየጨቆነና እያስጨነቀ ሌላውን ጸረ-ሰላም የሚል ቀልደኛ የሆነ የቦዘኔዎች ስብስብ ነው። ይህንን የወንበዴ ቡድን ደግሞ ዛሬ ላይ ቆመው እንደ መንግስት የሚቆጥሩ ካሉ ወይ አውቀው የተኙ አልያም የየዋሆች የዋህ ናቸው። እንደዛ አይነቶቹን ደግሞ ሊያድን የሚችለው የፈጠራቸው ብቻ ነውና የኛ መልክት ለነቁቱ ነው።

የነቁትን ተነሱ እንላለን፤ አገራችን መሳለቂያ እና የቦዘኔዎች መጨፈሪያ መሆኗ ያብቃ። ተባብረን እንነሳና በእውነት እና በውሸት መካከል ያለውን መስመር እናድምቅ!

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኦነግ አባልነት እየሰከሰሰ በኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰውን ግፍ እንደቀጠለ ነው

የወያኔ አገዛዝ የቀድሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋካልቲ ዲን የነበሩትን አቶ አበራ ደገፉን ጨምሮ በአራት ኦሮሞ ተከሳሾች ላይ የጥፋተኛነት ብይን ማሰጠቱን ለማወቅ ተችሏል።

በግለሰቦቹ ላይ የተደረገው ክስ “የጥላቻ መልክት በማሰራጨት፣ ወጣቶችን በመመልመል፤ ከህገ ወጡ የኦነግ ድረጅት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል” የሚል እንደሆነም ታውቋል። ከጥፋተኛ ተብዬዎቹ ሌላው አቶ ቶሎሳ ወልዴ የተባሉና ለረዥም አመታት በጠበቃነት የሰሩ ግለሰብ ናቸው።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑትን አቶ አበራ ደገፉን የሚያውቁ ግለሰብ ለዝግጅት ክፍላችን ባስተላለፉት መልክት፤ ግለሰቡ በአቶ መረራ ጉዲና የሚመራው የኦሮሞ ህዝብ ብሔራዊ ኮንግረስ ፓርቲ አባል ነበሩ።

በአገሪቱ ውስጥ ዋና ህግ ሰባሪ የሆነውና የህግ ተቋማትን ለግፍ ማስፈጸሚያነት የሚጠቀመው የወያኔ አገዛዝ፤ በህጋዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የሚሳተፉ ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ ደረጃ እና ተሰሚነት የሚጠላቸውን ኦሮሞዎች በኦነግ አባልነት እየከሰሰ ለእስር እና ለሞት ፍርድ እንደሚዳርግ ይታወቃል።

## ሶስት ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ቡድኖች ጥምረት መመስረታቸው ታወቀ

ሶስት የተቃዋሚ ቡድኖች ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነት እና ለፍትህ በኢትዮጵያን መመስረታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መግለጫ ገልጸዋል።

ድርጅቶቹም፥ የአፋር ህዝብ ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የአንድነት እና የፍትህ ንቅናቄ፤ እና ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ መሆናቸው ታውቋል።

ጥምረቱ በሰጠው መግለጫ፥ "መሰረተ-ሰፊ የሆነና ሁሉን አቀፍ የአትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ምስረታ፣ ዘረኛውንና አምባገነናዊ የሆነውን የወያኔ አገዛዘ ማስወገጃ፣ ዘለቄታነት ያለው ሰላም ማስፈኛ፣ የሁሉም አይነት መብቶች፣ ነጻነቶችና የብሄራዊ አንድነትና ጥቅም ማስከበሪያ፣ የኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ ፍትህ መቀዳጃ ፍቱን መሳሪያ መሆኑን ከልብ በመቀበል" እንደተመሰረተ አስረድቷል። ለሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት ምስረታ ተግቶ እንደሚሰራም ቃል ገብቷል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለመጪው አምስት መታት ያወጣው እቅድ ባዶ ህልም ነው ተባለ

አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው እና በቀድሞ የአዲስ ነገር ጋዜጣ ሰራተኞች የተመሰረተው የመረጃ ድረ-ገጽ ባወጣው የኢኮኖሚ ትንታኔ ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለመጪው አምስት አመታት ያወጣውን እቅድ "ባዶ ህልም" ብሎታል።

አቶ ዘሪሁን ተስፋዬ የተባሉት የኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ተንታኝ ባቀረቡት በዚህ ጽሁፍ፥ ወያኔ "እድገት እና ትራንስፎርሜሽን" የሚል ስያሜ የሰጠው እቅድ ተገቢውን የኢኮኖሚ ትንበያ ሞዴል ያልከተለ እና በብዙ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል የሚነገርለት ነው ብለዋል። አገዛዙ እቅዱን በሚመለከት ህዝባዊ ውይይት በማድረግ ስም የአዲስ አበባን ነዋሪዎች ለግዳጅ ስብሰባ መጥራቱም ታውቋል።

የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሆነው የወያኔ ሹመኛ ጁነዲን ሳዶ አገዛዙ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ሊሰራ ካቀዳቸው ተግባራት አንዱ 8000 ኪሎሜትር የባቡር ሃዲድ መገንባት እንደሆነና፤ በየአመት 1600 ኪሎ ሜትር የሚሆነውን በመገንባት እቅዱ ግቡን እንደሚመታም መናገሩን ጸሃፊው አስፍረዋል። አቶ ዘሪሁን አገዛዙ ከዚህ ረገድ ከዚህ ቀደም ያስመዘገበው ስኬታማነት ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልጹ፥ የዛሬ ሶስት አመት 114 ኪሎሜትር የሚሆነውን የኢትዮ-ጅቡቲ የሃዲድ መስመር ለማደስ እቅድ ወጥቶ፤ ዛሬ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆነው የፕሮጀክቱ ክፍል እንዳልተጠናቀቀ ገልጸዋል።

"ይሁን እንጂ" ይላሉ ጸሃፊው፥ "የአሁኑ እቅዳቸው ስኬታማ እንደሚሆን ጠንቋይ የተነበየ ይመስል ደጋግመው ለህዝቡ እየተናገሩት ነው"።

መለስ ዜናዊ ከአምስት አመታት በፊት በሶስት አመታት ጊዜ ውስጥ የአገሪቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ሽፋን መቶ በመቶ እንደሚሆን መናገሩ ይታወሳል። ዛሬ፥ ከአምስት አመታት በኋላ ግን ያ ቁጥር 0.4 በመቶ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህም በተጨማሪ፥ ዘረኛው አምባገነን የዛሬ ሃያ አመት ገደማ የኢትዮጵያ ህዝብ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ በቀን ሶስት ጊዜ መመገብ እንደሚጀምር ከመናገር አንስቶ፤ በቅርብ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ የዔሌክትሪክ ሃይል ስለሚትረፈረፍ ከዚህ በኋላ ሻማ የሚበራው ለልደት ብቻ ነው ማለቱ አይረሳም።

## ከግቤ አንድ ግድብ በግድ የለሽነት በተለቀቀ ውሃ ዜጎች መፈናቀላቸው ታወቀ

ከግቤ አንድ የሃይል ማመንጫ ጣቢያ በግድ-የለሽ አሰራር ምክንያት የተለቀቀ ውሃ ጎርፍ ሆኖ ነዋሪዎችን ማፈናቀሉን ለወያኔ አገዛዝ ቅርበት ያለው ሪፖርተር ጋዜጣ ዘግቧል።

የሃይል ጣቢያው ካለው ትራንስፎርመሮች መካከል አንዱ በመቃጠሉ፤ ጣቢያው ከሚያመርተው ሃይል አንድ ሶስተኛ የሚሆነው እየተመረተ እንዳይደለ፤ በዛም ምክንያት ያንን ሃይል ሊያመርት የነበረው ውሃ በግድቡ ውስጥ ታቁሮ እንደቀረ እና የክረምት ዝናብ ሲጨመርበት ግድቡ ሊይዘው ከሚችለው በላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽንም ግድቡን ለማስተንፈስ በሚል ውሃውን እንደለቀቀ እና ይህም ጎርፍ ሆኖ የአካባቢውን አርሶአደሮች ማፈናቀሉን ሪፖርተር ዘግቧል። ጋዜጣው አናገርኳቸው የሚላቸው ባለሙያዎች እንደገለጹት፣ ችግሩ የተፈጠረው ኮርፖሬሽኑ የተቃጠለውን ትራንስፎርመር በጊዜ ባለማስለወጡ ነው።

የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ ልማት እንዳለ ለማስመሰል እና ለባለስልጣናቱ እና ለደጋፊዎቹ የሙስናን በር ለመክፈት ሲል በቂ ጥናት ያልተደረገባቸውን ፕሮጀክቶች በግድ-የለሽነት እንደሚያካሂድ ተደጋጋሚ ወቀሳ ይቀርብበታል። በአሁኑ ሰዓት በቢሊየኖች የሚቆጠር ብር የወጣበት የጊቤ ቁጥር ሁለት ግድብ በመደርመሱ እንደገና እየተገነባ መሆኑ ይታወቃል።

## የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ የመረጃ ምንጮቹን እንዲያሳውቅ በወያኔ አገዛዝ መታዘዙን ገለጸ

በኢትዮጵያ ውስጥ ከቀሩት እና በከፍተኛ አፈና ስር በመጠኑም ቢሆን ከሚንቀሳቀሱት ጥቂት ገለልተኛ የግል ጋዜጣዎች ውስጥ አንዱ የሆነው አውራምባ ታይምስ በወያኔ አገዛዝ ህገ-ወጥ ትእዛዝ እንደተሰጠው ሐሙስ እለት በድረ-ገጹ ላይ ባወጣው ጽሁፍ አስታውቋል።

በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ደስታ ተስፋው ጋዜጣው ለዜና ዘገባ የሚጠቀምባቸውን የመረጃ ምንጮች እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ እንዲያሳውቅ ትእዛዝ ሰጥቷል።

"በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት መሠረት አንድ ጋዜጠኛ ለፍርድ ቤቶች ሳይቀር የመረጃ ምንጭ የማሳወቅ ግዴታ እንደሌለበት በግልጽ የተደነገገ ቢሆንም ብሮድካስት ባለስልጣን በ‹ሬጉላቶሪ› ሽፋን ሕገ መንግስቱን የሚጥስ ጥያቄ መጠየቁ የጋዜጣው ባልደረቦችን አስገርሟል፡፡" ሲል አውራምባ ታይምስ በድረ-ገጹ ባሰፈረው ዘገባ ገልጿል።

"ከዚህ በተጨማሪ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ሀላፊነት ውጪ ጋዜጣው ከሽያጭና ከማስታወቂያ የሚያገኘውን የፋይናንስ ሪፖርት እንዲያሳውቅ የጠየቀ ሲሆን ይህን የመጠየቅ ኃላፊነት የተጣለበት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መሆኑ እየታወቀ ብሮድካሰት ባለስልጣን ይህንን መጠየቁ ብዙዎችን አስገርሟል፤" ብሏል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org